# ‘ፍርሀቴን አቃጠልኩት’ ለየኔሰው ገብሬ የተፃፈ

ዳኛቸው ቢያድግልኝ

እነሆ አርባኛው ቀንህ በካህናት ፀሎት ተነሳ። በመላው ዓለም የተበተኑ ወገኖችህም ስምህን ከፍ አድርገው አወደሱ። የጠበሰህ እሳት ከሚያሰማህ ስቃይና ሕመም ይልቅ ትግራይ በቀል ጠላቶችህ እንዲሁም ሆዳምና አድርባዮች የሚያደርሱብን በደልና ግፍ ይበልጥ እንዳሳመመህ ነገርካቸው። ከነፃነት እጦት ሞት እንደሚሻል መራር ሞት ሞተህም አሳየሃቸው። የዘርን አጥር ሰብረህ፣ የጎጥ ፖለቲካን ኮንነህ ኢትዮጵያውያን እንደ ሕዝብ ነፃነትን እንደሚሹ አስተምረህ አለፍክ። ታጋዮች በስምህ ተማምለው ተነሱ። ገጣሚዎች ስምህን ከፍ እያደረጉ ተቀኙ።

*“እንደ ትንግርት ራዕይ የመለኮት ጸጋ፣*
*ሰብስበህ አሰርከው አበሻን ባንድጋ።*
*ቆራጥ መስዋዕትነት ቢሹት የማይገኝ፣*
*ሞትህ ያገር ልደት ሊሆን ነው መሰለኝ።....”*[1]

ለአንተ ሞት ምክንያት የሆኑት ወያኔን እድሜ የሚሰጡ ከየመንደሩ የወጡ ሆድ አደሮች መሆናቸውን አስብ ዘንድ ብርታት ሆንከኝ። ባንተ ሞት የተሳለቁ እኒህ ትራፊ ለቃሚዎች እኔም ዘንድ አሉ። ለኔም ሞት እንደማይመለሱ አውቃለሁ። ቀን ከሌት የስለላ ዶሴ እያመላለሱ የራሳቸውን የውርደት ሞት የሚጠብቁ ብዙ ናቸው። ውስጣቸው ባዶ የሆነ፣ በፍርሀት የተሸማቀቁና ጊዜያዊ ጥቅም የደለላቸው ወይም ራሳቸውን ለማዳን በሌላው ሕይወት ገበጣ የሚጫወቱ በያገሩ በየመንደሩ አሉ። እኒህ አሾክሻኪዎችንና እበላ ባዮችን ግን አጥብቄ እፈራ ነበር። ለመኖር ሲሉ ወይም ለመታመን ሲሉ ብዙ መዘዝ ያመጣሉ እያልኩም አስብ ነበር። ቤተሰቦቼና የቅርብ ወዳጆቼም በኔ ምክንያት ሊደርስባቸው የሚችለውን ሳስብ ‘ጎመን በጤና’ እያልኩኝ ‘ባገር የመጣ ነውና ምን ይደረጋል’ በሚል ፈሊጥ ፍርሀቴን ሳባብለው ነበር የኖርኩት።

የቀረኝ መሸሸጊያ ቤተክርስትያን ነው ብዬ በፀሎትም ለመትጋት ሞከርኩ። ግን ቤተክርስቲያኒቱም ታወከች። አስተዳደሩ የወያኔ፣ ቤተክህነቱ የሰላዮችና የታጣቂዎች ታዛ ሆነ። የጣልያንና የእንግሊዝ ቅኝ ገዢዎች እንዳደረጉት ሁሉ ወያኔዎችም ሀይማኖት አፍርሰው ቤተክርስቲያናትንና መስጊዶችን ዋሻቸው አደረጉ። ጣልያን ባበጀው ካርታ አገሪቱን በቁጥር ሸነሸኑ። ቢቸግረኝ መሮጥ ያዝኩኝ ክፋትን የሁዋልዮሽ እያየሁ፣ ጎጠኝነትን ላይደርስብኝ እየተፈተለኩ አመለጥኩ። ስደትን እንደ አሸናፊነት ቆጥሬ ተገላገልኩ ስል ለካስ ጎጠኝነት፣ክፋትና ጥላቻም ወያኔ በቆረጠላቸው ትኬት ቀድመውኝ ገብተዋል። የስደት ምድርም የወያኔ ዳንኪራ መምቻ ነው።

ባገር የመጣ ነው እል የነበረውን በአለም ያለ ነው እያልኩ ለኑሮዬ ደፋ ቀና ማለቱን ቀጠልኩ። ሀሳቤን እርግፍ አድርጌ ከሲታውን ጎኔን እጠግነው ገባሁ። ሳይክል ላይ ወጥቼ የማላውቅ ሰው ቆንጆ መኪናም እነዳ ጀመር። እንዳይቀርብኝ ፖለቲከኞችንን እያንኳሰስኩ የፖለቲካ አዋቂ መምሰሉን ደግሞ ቀጠልኩበት። አበሻ እንደሁ ዞሮ ዞሮ ያቺኑ ነውና የሚያወራው አዋቂ መምሰል ያስከብራል። ጠጠር ያለ ነገርና ተሳትፎን የሚሻ ጉዳይ ሲነሳ ጨዋታ መቀየር ልማዴ ሆኖ ነበር። እኛ ዘንድ ሁሉንም መስሎ ማደርና ራስን ያለመሆን የጠቢብ ያህል የሚያስከብር የጥሩ ሰው መለኪያ ነው። ዝቅጠትን አገዝፈን ንቅዘትን አሸሞንሙነን ያልሆንነውን ሆነን መኖር እኮ ከመቃብር በላይ ለማይውል ስም መትጋት መሆኑን ልብም አላልነውም። እውነትን ፈርተን በባዶነት ኮርተን የሞተ ኮንነን እድሜያችንን እንገፋዋለን። ራሳችንን ሆነን ላለመኖር የተማማልን ይመስላል። አንተ ግን ገና ሃያዎቹን ሳትጨርስ ትግልህን አጠናቀቅህ የማይጠፋውን እሳት አቀጣጠልክ።

በሞትህ ሲሳለቁበት ግን ልቤ ደማ ላንተ ሳይሆን ለራሴው አለቀስኩ። እናም አሁንስ በቃኝ ለማለት ተገደድኩ፣ ለራሴው መሞቻ ጥይት መግዣውን በቁሜ ለመክፈል ከወያኔ ጋር መሻቀጤ ይዘገንነኛል። ፈሪ በመሆኔ ያለሁበት ድረስ እየመጡ የሚያላግጡብኝ አበሳጨኝ። ስግብግብ በመሆኔ ደክሜ ያመጣሁትን ገንዘብ በኢንቨስትመንት ስም ሲወስዱብኝ እኔው ራሴ እንደሌባ አፈርኩ። በአንተና በእኔ መካከል ያለውን ልዩነት በዘመናት እንኳን መተመን አልቻልኩም። በህልፈትህ ግን ዳንኩኝ በቆራጥነትህ ደግሞ ድፍረትን አገኘሁኝ።

ወንድሜ የኔ ሰው ሆይ ያንተ መቃጠል ያቃጠለው የሞት የመኮነን ጠባዬን ነው። አዎን ወንድሜ እኔ እኮ በሚያብበውና ፍሬ በሚሰጠው ሳይሆን ወድቆ በሚበሰብሰው የነገር ቃርሚያ ላይ የማጠፋው ጊዜ ነበር የሚበዛው። በሚሆነው ወይም መሆን

ባለበት እንጂ ሳይሆን በቀረው ላይ መታከቴ እንዲሁ መኖሬን ለማሳወቅ የማደርገው ጫጫታ መሆኑን አመንኩ። ስለ አመንኩም የቀድሞውን ራሴን ተጠየፍኩ። በትንሽም ይሁን በትልቅ ጉዳይ የኔን የድርሻዬን ለማድረግ እንጂ የድርሻቸውን ስላላበረከቱት አልወቅስም ብዬ ቆርጫለሁ። በሞትህ እንደወያኔ ዳር ቆሜ ላላግጥ ደግሞ ቃል እገባልሃለሁ። አባንግ ነበር ‘ዱ የናንተን ድርሻ’ ሲለን የነበረው? አዎን የኔን ድርሻ እኔው አበረክታለሁ።

ወንድሜ የኔ ሰው ሆይ ያንተ መቃጠል የኔን ባዶ ኩራት አቃጥለው ዘንድ አደፋፍሮኛል ወደር ያጣውን ፍርሀቴን በአንተው እሳት አቃጠልኩት። በውጭ እየኖርኩ ብዙ ማድረግም እየቻልኩ የሀገሬን ጉዳይ የቡና ወሬ ማድረጌ አሳፍሮኛል። ቢንቁኝ እውነት አላቸው፤ ቢያዋርዱኝም ተገቢ ነው። ምክንያቱም ለራሴ ክብር ለኔው ነፃነት አልቆምኩም ነበርና። ከዚህ በሁዋላ ግን ያለ ጠያቂ ያለ ቀስቃሽ እነሳለሁ። ሞትህን ከንቱ አድረጌ ጥሪህን አልሰማሁም ብል ለትውልድ የሚተርፍ ወንጀል እንደምሰራ አምናለሁ። በምድር የሰጠኸኝን አደራ በሰማይ ትቀበለኝ ዘንድ በእግዚአብሄር ስም ቃል እገባልሃለው።

ውድ የኔሰው ያንተ ቤዛ መሆን የስንቱን ህይወት ይቀይረው እንደሆን አላውቅም። የኔ ግን ለነፃነት ይቆማል፣ ማንንም አይጠብቅም። የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል በዚያች ሀገር ባንዲራዋ ከነሙሉ ክብርዋ እስኪውለበለብ ይታገላል። የቀድሞው እኔነቴ ላይመለስ ሄዷል። እነሆ በሞትህ ያደረግኸው ይህንን ነው። እኔ ወዳንተ ስመጣ ጥሪዬን አልሰማህም ሞቴን ከንቱ አደረግኸው ብለህ እንደማትወቅሰኝ አምናለሁ። የአልጄርያውን መሀመድ ቦዛዚ ካገኘኸው አበሻም ይነሳል በለው። ሲነሳ ደግሞ ዳግም ጎጠኛነት፣ ዳግም አምባገነንነት በምድሪቱ አይኖርም በለው። እስከዚያው እግዚአበሄር ነብስህን በገነት ያኑርልኝ።

ያንተው

ዳኛቸው ቢያድግልኝ

biyadegelgne@hotmail.com

[1] ከጌታቸው አበራ የተቀነጨበ ስንኝ http://www.ethiomedia.com/broad/lememhir_yenesew.pdf